አንበሳ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ.

LION INTERNATIONAL BANK S.C.

ታህሳስ 11/2012 ዓ.ም

## የባለአክስዮኖች 15ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤን አስመልክቶ

## ከአንበሳ ኢንተርናሽናል ባንክ የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ

አንበሳ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ በ2011 በጀት ዓመት ከታክስ በፊት ብር 695.5 ሚልዮን ማትረፍ የቻለ ሲሆን፤ የተመዘገበው ትርፍ ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር የብር 215 ሚሊዮን ወይም የ45 በመቶ ብልጫ አለው፡፡

ባንኩ በሁሉም የተቀማጭ ሂሳብ ዓይነቶች 4.8 ቢሊዮን ብር ማሰባሰብ የቻለ ሲሆን፤ አጠቃላይ የባንኩ ተቀማጭ ገንዘብ (Deposit) መጠን 16.4 ቢልየን ብር ደርሷል፡፡ የተቀማጭ ገንዘብ ማሰባሰብ አፈፃፀሙ ካለፈው ዓመት የ41 በመቶ ዕድገት አሳይቷል፡፡ ይህ አበረታች ውጤት ሊገኝ የቻለው የባንኩ አገልግሎት አሰጣጥ በእጅጉ በማሻሻል የደንበኞቹን ቁጥር ከ794 ሺህ በላይ እንዲሆን በመቻሉ ነው፡፡

ባንኩ በተጠናቀቀው የበጀት ዓመት ከወጪ ንግድና ከሌሎች ዓለም አቀፍ የንግድ እንቅስቃሴዎች 219 ሚሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሪ ያገኘ ሲሆን፤ አፈጻጸሙ ካለፈው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር በ 101 ሚሊዮን ዶላር ወይም በ86 በመቶ ዕድገት ማስመዝገብ ችሏል፡፡ ከተገኘው ገቢ ውስጥ 75 በመቶ ከውጪ ንግድ ዘርፍ የተገኘ ነው፡፡

የባንኩን የብድር ስርጭት በተለያየ ክፍለ ኢኮኖሚ ለተሰማሩ ደንበኞቹ 3.8 ቢሊዮን ብር የብድር አቅርቦት በመስጠት፤ አጠቃላይ የብድር ክምችት መጠኑ ወደ 11.6 ቢሊየን ብር ከፍ ማድረግ ተችሏል፡፡ በብድር አመላለስ ረገድም በበጀት ዓመቱ ብር 3.5 ቢልየን ተመላሽ ገንዘብ ማሰባሰብ ተችሏል፡፡

ባንኩ በበጀት ዓመቱ ባደረገው የኦፐሬሽን እንቅስቃሴ ብር 2.3 ቢሊዮን አጠቃላይ ገቢ በማግኘት ካለፈው ዓመት በ772 ሚሊዮን ብር ወይም የ50 በመቶ ብልጫ ያለው አፈጻጸም ለማሳየት

ችሏል። በዚህም በበጀት ዓመቱ ማጠቃለያ ከታክስ በፊት ብር 695.5 ሚልየን ብር ለማግኘት ችሏል።

| መግለጫ | የበጀት ዓመት | | ዓመታዊ ዕድገት በፐርሰንት |
|---|---|---|---|
| | 2010 | 2011 | |
| ተቀማጭ ገንዘብ(ዲፖዚት) | 11.6 ሚሊዮን ብር | 16.4 ሚሊዮን ብር | 41% |
| የውጭ ምንዛሪ | 118 ሚሊዮን ዶላር | 219 ሚሊዮን ዶላር | 86% |
| ትርፍ | 480 ሚሊዮን ብር | 695.5 ሚሊዮን ብር | 45% |
| የደንበኛ ቁጥር | 590,637 | 794,057 | 34% |
| ቅርንጫፍ | 190 | 229 | 21% |
| ገቢ | 1.6 ሚሊዮን ብር | 2.3 ሚሊዮን ብር | 50% |

ባንኩ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የቅርንጫፎቹን ብዛት ወደ 229 በማድረስ አገልግሎት በመስጠት ላይ ሲሆን፤ የባንክ አገልግሎቱን ይበልጥ ተደራሽ ለማድረግ ቅርንጫፎቹ ባልተዳረሱበት አካባቢዎች በመለመላቸው 1,756 የኤጀንት ባንኪንግ ወኪሎች እና "አንበሳ ሄሎ ካሽ" በተሰኘ የሞባይል ባንኪንግ አገልግሎት አማካይነት ከ202,834 ለሚበልጡ ደንበኞችን አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።

በተጨማሪም ባንኩ እየሰጠ ባለው የካርድ ባንኪንግ አገልግሎት ከ49 ሺህ በላይ ደንበኞች የኤ.ቲ.ኤም አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ የተቻለ ሲሆን፤ በቅርቡ የኢንተርኔት ባንኪንግ አገልግሎት ለመስጠት ዝግጅቱ አጠናቋል።

በበበጀት ዓበቱ መጨረሻ የባንኩ አጠቃላይ ሃብት (Asset) ብር 20.2 ቢሊየን የደረሰ ሲሆን፤ አጠቃላይ ካፒታሉና ህጋዊ መጠባበቂያ ገንዘብ ብር 2.6 ቢሊየን ደርሷል።

ከዚሁ ጎን ለጎን ባንኩ ለ4,599 ቋሚ እና ጊዜያዊ ሰራተኞች የስራ ዕድል የፈጠረ ሲሆን፤ የሰራተኞቹን ዓቅምና ክህሎት ከማጎልበት አንጻር ለ3,226 ሠራተኞች ልዩ ልዩ ስልጠናዎች ሰጥቷል። እንዲሁም 44 ቋሚ ሰራተኞቹ ሙሉ የትምህርት ወጪያቸውን በመሸፈን በመጀመሪያና ሁለተኛ ዲግሪ መርሃግብሮች ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ በማድረግ ላይ ይገኛል።

***አንበሳ ኢንተርናሽናል ባንክ***

***የስኬትዎ አጋር!***